## በትውልድ ሃገሬ የ TB ክትባት (BCG) ተከትቤ ነበር። አሁንም TB ልያዝ እችላለሁ?




የ TB ክትባት የተከተቡ ሰዎች አሁንም TB ሊይዛቸው ይችላል።

የ TB ክትባት ጥበቃ **በጊዜ ብዛት ሊጠፋ ይችላል**።

ክትባቱን ተከትበው ቢሆን እንኳን፣ አዎንታዊ የደም ምርመራ ውጤት ማለት LTBI አለብዎት ማለት ነው።

የLTBI መድሃኒት **መውሰድ** ንቁ ከሆነ TB **ይጠብቅዎታል**።

## በ LTBI መያዜ የስደተኛ ማመልከቻዬን ያዘገየዋል?

ለ LTBI መድሃኒት መውሰድ ማመልከቻዎን **አያዘገየውም** ።

የስደተኛ ሃኪምዎ LTBI እንዳለብዎት ለጤና መምሪያዎ የሚያሳውቅ ይሆናል።

የአካባቢ የጤና መምሪያ ድጋፍ ለመስጠት ሊያገኝዎት ይችላል።

ለ LTBI መድሃኒትዎን ማዘዝ የሚችል ሃኪም ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ፣ ወደ አካባቢዎ የጤና መምሪያ ይደውሉ:-

**አውራጃ፡-** ______________________

**ስልክ ቁጥር፡-** ______________________

የተላላፊ በሽታ ጥናት፣ መከላከል እና ቁጥጥር
ፖስታ ሳጥን 64975፣ St. Paul, MN 55164
651-201-5414 ወይም 1-877-676-5414
www.health.state.mn.us

1/2024

# በድብቅ የሳንባ ነቀርሳ (LTBI) መያዝ ለእኔ ምን ማለት ነው?



**LTBI ማከም እና እርስዎን እና የሚወዷቸውን ከመታመም ማስቆም ይችላሉ።**

DEPARTMENT OF HEALTH

በካሊፎርኒያ የሳንባ ነቀርሳ ተቆጣጣሪ ማህበር ፈቃድ የተወሰደ።

## LTBI ምንድን ነው?
## እንዴት ሊይዘኝ ቻለ?

LTBI በሰውነትዎ ውስጥ ድብቅ በሆኑ (ወይም የተኙ) የ TB ጀርሞችን የያዘ ኢንፌክሽን ነው።

LTBI የያዝዎት ንቁ በሆነ TB ታሞ ከነበረ ሰው ጋር **አየር በመጋራትዎ** ነበር።

የ TB ክትባት ቢከተቡም አሁንም LTBI ሊይዝዎት ይችላል።

## በLTBI እና ንቁ በሆነ TB መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ፡-

| **LTBI** የያዘው ሰው፡- | **ንቁ የሆነ TB** የያዘው ሰው፡- |
|---|---|
| ህመም አይሰማውም | ህመም ሊሰማው ይችላል |
| መደበኛ የደረት ራጅ አለው | መደበኛ ያልሆነ ራጅ ሊኖረው ይችላል |
| **የ TB ጀርሞችን** ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ አይችልም | **የ TB ጀርሞችን** ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ይችላል |
| ህክምና ንቁ የሆነ TBን መከላከል ይችላል | ህክምና ንቁ የሆነ TBን ማዳን ይችላል |
| ህክምናው አጭር **(ከሶስት እስከ አራት ወራት)** እና ቀላል ነው | ህክምናው ረዘም ያለ ነው **(ከስድስት እስከ 12 ወራት ወይም ከዚያ በላይ)** |

## ለ LTBI መድሃኒት ልወስድ የሚገባው ለምንድን ነው?

ለ LTBI መድሃኒ ካልወሰዱ፣ ንቁ የሆነ TB የመሆን እድል አለው።




ንቁ የሆነ TB በጣም ሊያሳምምዎ የሚችል **ከባድ በሽታ** ነው።



**ንቁ በሆነ TB** ከተያዙ ሰዎች ግማሽ የሚሆኑት **ሆስፒታል ገብተዋል።**

5%

ንቁ በሆነ TB **ከተያዙ ሰዎች በበሽታው ሞተዋል።**

## ለLTBI መድሃኒት ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

**የስደተኛ ሃኪሙ መድሃኒት ሊያዙልዎት ይችሉ እንደሆን** ይጠይቁ።

የማይችሉ ከሆነ፣**ወደ መደበኛ ሃኪምዎ ሄደው መድሃኒት** እንዲያዙልዎት ይጠይቋቸው። የእርስዎን የደም ምርመራ የጽሁፍ ስራ ይዘው ይምጡ።

እንዲሁም ለህክምና ወደ ክሊኒክ እንዲልክዎ የአካባቢዎን የጤና መምሪያ ማነጋገር ይችላሉ።

**መድሃኒቱን ካልወሰዱ፣ የእርስዎ LTBI ንቁ የሆነ TB የሚሆንበት እድል** ከአስር አንድ ነው።

**ንቁ በሆነ TB ከመያዝ እንዲሁም ወደ የሚወዷቸው ሰዎች ከማስተላለፍ ራስዎን ይጠብቁ።**